# በእስራኤል በሚገኘው የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት

- የኢትዮጵያዊያንን ሕብረተሰብ የሚያስፈልጋቸው ነገሮችንና ያሉላቸው ፕሮግራሞች በጥንቃቄ ሲጠና ሰፋ ያለ ውይይትና ምክር ታግዞ፤ የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ጥረቱና ትኩረቱ ዕድሜያቸው ከ13 እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያሉትን ወጣቶች ላይ መሆን እንዳለበት ወሰነ:: በ2004 ዓ.ም SPACE (ስፔስ) በመባል የሚጠራውን የትምሕርት ማጠናከሪያና በየትምህርት ቤቱ የ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና የማዘጋጃ ትምህርት ፕሮግራም በሥራ ላይ አዋለ:: በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች ፈለጎ ማግኘትና እንክብካቤ መስጠት፤ ሕብረተሰብን መግንባት የዓመታት ዕቅዶችን ዘርግቶ ኢትዮጵያዊያን ያላቸውን ችሎታ ሙሉ በሙሉ መጠቀም እንዲችሉ ጥራት ያለው ዕድል ለመስጠት የታቀደ ነው:: የ"ብሮኪድይል" የሚባለው ተቋም ጥናት እንደሚያሳይው እነዚህ ፕሮግራሞች ገንቢ ተፅኖ እንዳላቸው ያሳያል::

- የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት የሥራ እንቅስቃሴ በጀት ከሰሜን አሜሪካ ይሁዲ አንድነት ድርጅት(JFNA)፣ የእስራኤል መንግሥት፣(ሚስራድ ሃቅሊታ፣ የትምህርት ሚኒስቴርና የገንዘብ ሚኒስቴር)፣ ሶህኑት ሃይሁዲት፣ ጆይንት ይስራኤልና ኬሬን ሃይሶድ የተወጣጣ ነው::
  እነዚህም መሥሪያ ቤቶች የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ድጋፍ በመቀጠል፤ እያንዳንዳቸውም የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት እጅግ አስፈላጊነቱን በመግለፅና የሚሠራውን ሥራዎችን ያያሉ::

- እስከ አሁን ድረስ 29 ከተማዎች የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት እንቅስቃሴዎች ተጠቃሚ ሆነዋል፤ ይኸውም:- ዓፉላ፣ ቤኤር ሼባዓ፣ ገደራ፣ ኽደራ፣ ክርያት ጋት፣ ክርያት ማላዓኪ፣ ሉድ፣ ናታንያ፣ ርሆቮት፣ ራምሌ፣ ዓራድ፣ ቤት ሼሜሽ፣ አሽኮሎን፣ አሽዶድ፣ ፔታህ ቲክቫ፣ ሲድሮት፣ ክርያት ቢያሊክ፣ ክርያት ሞፅኪን፣ ክርያት ያም፣ ቲራት ሃካርሜል፣ ቤት ሽዓን፣ ሚግዳል ሃዒሜክ፣ ነፀሪት ዒሊት፣ ኢየሩሳሌም፣ ሃይፋ የክናዓምና ፓርዳስ ሃና ናቸው:: የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት SPACE (ስፔስ) ፕሮግራም የሚያካትታቸው
  ሀ/ ለተማሪዎች የትምሕርት ዕገዛ መስጠት
  ለ/ የትምህርት ቤት አገናኝ ሠራተኞች እንዲኖሩ ማድረግ
  ሐ/ ለከፍተኛ ትምሕርት ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ መስጠት
  መ/ የወጣቶች ማዕከል

ዛሬም የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት አመካኝነት በዓለም ዙሪያ ለሚገኙት ይሁዳዊያን የኢትዮጵያዊ አዲስ ገቢዎችን ለመገንባትና ለማበልጸግ እንዲሁም ያላቸውን ችሎታ ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ዕድል ይሠጣል:: ከዚያም ሕብረተሰቡ ለእስራኤል ሕብረተሰብ አስተዋፆ ያበረክታል::

የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት መርሐ ግብር(ፕሮግራም) እንደሚከተለው ነው:-

1. SPACE (ስፔስ) ፕሮግራም

የኢትዮጵያዊያንን ሕብረተሰብ የሚያስፈልጋቸው ነገሮችንና ያሉላቸው ፕሮግራሞች በጥንቃቄ ሲጠና ሰፋ ያለ ውይይትና ምክር ታግዞ፤ የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ጥረቱና ትኩረቱ ዕድሜያቸው ከ13 እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ያሉትን ወጣቶች ላይ መሆን እንዳለበት ወሰነ:: በ2004 ዓ.ም SPACE (ስፔስ) በመባል የሚጠራውን የትምሕርት ማጠናከሪያና በየትምህርት ቤቱ የ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና የማዘጋጃ ትምህርት ፕሮግራም በሥራ ላይ አዋለ:: በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች ፈለጎ ማግኘትና እንክብካቤ መስጠት፤ ሕብረተሰብን መግንባት የዓመታት ዕቅዶችን ዘርግቶ ኢትዮጵያዊያን ያላቸውን ችሎታ ሙሉ በሙሉ መጠቀም እንዲችሉ ጥራት ያለው ዕድል ለመስጠት የታቀደ ነው::
የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት SPACE (ስፔስ) ፕሮግራም ሦስት ዋና ነገሮች ያካተተ ነው:- በትምሕርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች:- ለእያንዳንዱ የኢትዮጵያዊያን ተማሪ በአመርቂ ውጤት የ12ኛ ክፍል ትምህረቱን እንዲያጠናቅቅ ከዚያም በከፍተኛ ትምህርት ገብቶ ትምህርቱን ቀጥሎ በሥራ መስክ እንዲሰማራ ለማድረግ ሲሆን ይህም ከዚህ በታች በአሉት ፕሮግራሞች አመካኝነት ነው

- SPACE (ስፔስ):- የማጠናከሪያ ትምሕርትና የ12ኛው ማጠናቀቂ ፈተና ማዘጋጀት
- SPACE (ስፔስ):- ለስኬታማነቱ ተሳታፊዎች:- ትምሕርት ቤቶችና ቤተሰቦች ለምሳሌ ማሕበራዊና ትምህርታዊ አገናኝ ድልድይ ሆኖ ማገልገልና ለወላጆች አውደ-ጥናት መሥጠት::
- SPACE (ስፔስ):- ለከፍተኛ ትምሕርት ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ መስጠት

**በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች:-** አሳሳቢ እየሆነ የመጣውን ሕገ-ወጥ የሆኑ ወጣቶችንና የአደንዛዥ ዕፅ ተጠቃሚ ወጣቶችን ቁጥር እንዳያድግ መከላከል፤ እነዚህን ችግሮች ለመግታትና ለመቀነስ በወጣቶች ማዕከል አመካኝነት በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች ፈለጎ በማግኘት ከአልኮልና ከአደንዛዥ ዕፅ እንዲታቀቡ ትምህርት መስጠት::

**በመሪዎች አመካኝነት ማጠናከር:-** ኢትዮጵያዊያንን በማጠናከር ለዕድገት ማድረስ፤ ልምድ ያላቸውን መሪዎች በአገር አቀፍና በአካባቢ ያሉትን መሪዎች በማሰልጠን ሕብረተሰቡ ያለውን ችሎታ ሙሉ በሙሉ እንዲጠቀሙበት ለማድረግ መሪዎች አስተዎፆ እንዲያበረክቱ ማድረግ::

SPACE (ስፔስ) **ለትምህርት ቤት ተማሪዎች:-** ትምሕርታዊ ውድድር፣ የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ውጤትና የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ለከፍተኛ ትምሕርት፣ ለሥራና በእስራኤል ባለው ሕይዎት ሙሉ በሙሉ ለመሳተፍ መግቢያ ካርድ ናቸው:: የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ለመለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፤ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችና ወላጆቻቸውን በማግኘት ስኬታማ እንዲሆን የማጠናከሪያ ትምህርት እንዲያገኙ ምክርና አማራጮችን ያቀርባል፤ ድርጅቱም በውትድርናው መስክም

እንዲሳተፉ እርዳታውን ይለግሳል፤ ዓለማውም በዩኒቨርስቲ ገብተው አማርቂ ውጤት እንዲኖራቸው ለማድረግ የገንዘብ እርዳታ ይሠጣል::

ለትምህርት ቤት ተማሪዎች አምስት ፕሮግራሞችን ያካተተ ነው:-

- የ12ኛው ማጠናቀቂያ ፈተና ለማዘጋጀት የማጠናከሪያ ትምሕርት መስጠት
- ለወላጆች ዓውደ ጥናት መስጠት
- ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ እንዲኖር ማድረግ
- የብሔራዊ ውትድርና አገልግሎት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ
- ለከፍተኛ ትምሕርት ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ መስጠት

**የማጠናከሪያ ትምሕርት፡-** የማጠናከሪያ ትምሕርት ፕሮግራም ለየ12ኛው ማጠናቀቂያ ፈተና ለማዘጋጀት የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ጥረቱ ውጤታማ ተማሪዎችን ቁጥራቸውን ማበርከትና ውጤታቸውን የበለጠ ለማሻሻል ነው:: ፕሮግራሙም ትንሽ ተማሪዎችን በቡድን አድርጎ ተጨማሪ ጊዜ ትምህርት መስጠት ነው፤ ዓለማውም የትምህርት ውጤታቸው ማሻሻል ነው፤ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ደግሞ ለየ12ኛው ማጠናቀቂያ ፈተና ለማዘጋጀት ትምህርት መስጠት ነው ይህም ለፈተናው ቁልፍ በሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማጠናከር ሲሆን ለተማሪዎቹም በተጨማሪ ሰዓት በተከታታይ ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ነው::
የማጠናከሪያ ትምሕርት ፕሮግራም አመካኝነት የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት በስውር ትምህርታቸውን የሚያቋርጡትን ተማሪዎች ቁጥር ለመቀነስ ይጥራል:: ማለትም ተማሪዎች በትምህርታቸው እንዳሉ ሆኖ ነገር ግን በትምህርቱ ሂደት የማይሳተፉትን ሁሉ ለማለት ነው::

**2. ሕብረተሰቡን ማኀልበት፡-**
የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ለወላጆች አውደ-ጥናት ፕሮግራም በመዘርጋት ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት የበለጠ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው:: ይህም አስፈላጊና መሠረታዊ መረጃና ዕውቀት በማስገብየት የልጆቻቸውን ትምህርት ኃላፊነት እንዲወስዱ ድጋፍ ይሠጣል:: ይህም ፕሮግራም የእስራኤል የትምህርት ዘርፍ ምን እንደሚመስል ዕውቀት ያስጨብጣል:: ዓላማውም አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ወላጆች ጣልቃ እንዲገቡ ማስቻል ማለትም ይህም በትምህርት ዘርፉ ያለውን መብትና ግዴታ ግንዛቤ እንዲኖር ማጠናከር:: እንዲሁም ፕሮግራሙ ወላጆች የመጀመሪያ ቋንቋቸውን፣ የኢትዮጵያን ቅርስና ባህል በማስተማር ያላቸውን የማስተማር የሥራ ድርሻ ለማጠናከርም ነው::

- **ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ፡-** ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ ፕሮግራም የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ በትምህርት ዘርፍ ዕውቀት ያለቸውን፣ ማህበራዊ ጉዳይ ሠራተኞችንና የባሕል አገናኞችን በትምህርት ቤቶች እንዲኖሩ ማድረግ ነው:: እነዚህም የኢትዮጵዊያን ተማሪዎች ቁጥራቸው በርካታ ሆነው በሚገኙበት ትምህርት ቤቶች በየትምህርት ቤቱ ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ ይገኛሉ:: እነርሱም የወላጆች ተሳትፎ እንዲኖር ያበረታታሉ፤ እነርሱም ልጆችና የወላጆች ግንኙነት የተጠናከረ እንዲሆን ለማድረግ ወደ ቤት በመሄድ፣ በመንብኘትና በግል በመገናኘት ነው:: ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ ቋሚ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ያደርጋሉ፤ ወላጆችም በተለያዩ ዝግጅቶች ይኸውም:- ድግሶች፣ የባህል ግንኙነቶች የመሣሰሉት ናቸው:: ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ ሠራተኛውን ትምህርት

ቤቶች ሁሉ ዕርዳታውን የሚጠቀሙበት ነው:: እርሱም የባሕል ልዩነቶችን ያስረዳል፤ አልመግባባት ተፈጥሮ በተማሪው ላይ አፍራሽ አመለካከት እንዳይኖር ይከላከላል:: ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ ሠራተኞች የሙያ ሠራተኞችን በማግኘት ወጣቶች የሚያጋጥማቸውን ችግር ትኩረት እንዲሠጡት ያደርጋሉ:: እንዲሁም አፀፋቸው ከአለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ያደርጋሉ:: ትምህርታዊና ባሕላዊ አገናኝ ሠራተኞች ባለው ትምህርታዊና ማሕበራዊ ታህታይ መዋቅር መሠረት ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ድጋፍ ይሰጣሉ::

- **የሕብረተሰብ በመሪዎች (የድርጅት ወኪሎች)**:- የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ድግፍ ሥልጠና አማካኝነት የኢትዮጵያዊያን ሕብረተሰብ የወደፊት ሕይዎታቸውን በአስተማማኝ ሁኔታ ለመወሰን ከፍተኛ ሚና እንዲኖራቸው እንዲሁም ሕብረተሰቡ ለራሱና ለእስራኤል ለወጥ ለማምጣት ዕድል ይከፍታል::

የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት የሕብረተሰብ በመሪዎች ፕሮግራም ሁለት ፕሮግራሞችን አካትቷል

1. በአገር አቀፍና በአካባቢ ያሉትን መሪዎች ማሰልጠን
2. በሠፈር ያሉትን መሪዎች ማሰልጠን

**በአገር አቀፍና በአካባቢ ያሉትን መሪዎች ማሰልጠን**:- በአገር አቀፍና በአካባቢ ያሉትን መሪዎች ማሰልጠን የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት ከሕዝቡ የፈለቁ መሪዎች፣ የአካባቢ ተጠሪና አባል ኮሚቴዎች የድርጅት ወኪሎች እንዲሁም የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት የአገር አቀፍ መሪዎች በዚህ ፕሮግራም በአገር አቀፍና በአካባቢ ያሉትን የሕብረተሰቡን መሪዎች ዕወቀት፣ ገንዛቤና የህሊና ንቃት ያጎለምሳል:: ዓለማውም ትንሽ አስተዳደር ቡድኖችን በማሠልጠን የኢትዮጵያዊያን የበጎ ፍቃደኛ ድርጅቶችን ፍቱንነታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ነው:: እነዚህም ድርጅቶች የሕብረተሰቡን ጉዳዮች በማቅረብና በቀሰሙት ትምህርት ዕረዳትነት ለችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ከፍተኛ ሚና ይኖራቸዋል:: ፕሮግራሙም የሕብረተሰቡ አባሎች መሪዎችን ማፍራትና እንዲሁም የኢትዮጵያዊያን ሕብረተሰብ በአገሪቱ ባለው የኑሮ ሒደት ተሳትፏቸውን ያጠናክራል፤ በተጨማሪም ውስጣዊ ለውጥም እንዲፈጥር ያደርጋል::

**በአካባቢ ያሉትን መሪዎች ማሰልጠን ፕሮግራም**:- በርካታ የኢትዮጵያዊያን ሕብረተሰብ የሚኖሩት ድህነት በሠፈረባቸውና ብዛት ባለቸው በአዲስ ገቢዎች አካባቢዎች ነው:: በእነዚህ አካባቢዎች ብዙ ነገሮች ማለትም የኑሮ የጥራት ደረጃና ለኑዋሪዎች በአላቸው ዕድል ላይ እርብርብ ያስፈልገዋል:: ነገር ግን የእነዚህ አካባቢ ኑዋሪዎች የችግር ምንጭ የሆነው ለኢትዮጵያዊያን አዲስ ገቢዎች አስፈላጊ ነገሮችን ያለማዋቅና የግንዛቤ እጦት ነው::
እነርሱንም ለመርዳት ራሳቸውን አዲስ ገቢዎችን ጥሩ አድርጎ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፤ በዚህም አማካኝነት ያላቸውን ስጋትና ፍላጎቶች ማቅረብ ይቻላል:: እንዲሁም የአካባቢውን ችግሮች ለመፍታት፤ በሰፈሩና በአካባቢው ያለውን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ተሳታፊዎች ይሆናሉ:: እንዲሁም ደግሞም ኑዋሪዎች ራሳቸውን በተለያዩ ነገሮች ለማሻሻል እንዲችሉ ያበረታታል::

3. በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች:-
ዕርዳታ ለመጠየቅ የተሳናቸውን ወጣቶች አፈላልገን ለማግኘት እንጥራለን፤ ይህም እነርሱን ገንቢና ወደ መልካም ሁኔታዎች እንዲመለሱ ለመርዳት ነው፤ የአልኮልና

የአደንዛዥ ዕፅ አደገኝነትን በተመለከተ ሰፊ ትምህርት ይሰጣል፤ ከዚህም ጎን ለጎን እነዚህን መጥፎ ነገሮች የሚተካ ገንቢና ለሕይዎት አስፈላጊ ነገሮችን ትምህርት ይሠጣል::
የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች ችግሮች የሚቋቋመው እነዚህን ወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች አፈላልጎ መፍትሄና እንክብካቤ የሚሠጥበትን ማዕከል በማቋቋም ነው:: ይህ ማዕከል ለወጣቶቹ አንገብጋቢ ጉዳዮች ይህውም የአልኮልና የአደንዛዥ ዕፅ መጠቀም እንዲያቆሙ በቀጥታ መፍትሄ ለመስጠት ፕሮግራሞቹን ያቀርባል::

## በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች እንክብካቤ የሚሠጥበት ማዕከል

የኢትዮጵያዊያን ብሔራዊ ፕሮጀክት በመጥፎ አዝማሚያ ላይ የሚገኙትን ወጣቶች እንክብካቤ የሚሠጥበት ማዕከል ለእነዚህ ወጣቶች መጠለያ ያቀርባል፤ በዚህ ማዕከል የሚሠጡት አገልግሎቶች:- የባለሙያ ምክር፣ የአልኮልና የአደንዛዥ ዕፅ ከመጥቀም እንዲታቀቡ ማድረግና እርዳታ መሠጠት፣ እንዲሁም ዕርዳታ የሚሠጥበት የወጣቶች ለወጣቶች ስልክ መስመር ማዘጋጀት፤ ከዚህም በተጨማሪ ማዕከሉ አንባጓሮን በተመለከተና የግልን ሕይዎትና ስም ለመቀየር፣ የራስን ማንነት በተመለከተ፤ ለሕብረተሰቡና ለአገሪቱ ወገን ሆኖ ለመገኘት የሚያስችል ዓወደ-ጥናት ያቀርባል:: ማዕከሉም በውትደርና እንዲሳተፍ መረጃ እንዲሁም በፖሊስ ባለቸው ፋይልና በተለያዩ ችግሮች ምክኒያት ውትድርና ገብተው እንዳይሳተፉ የሚያግዳቸውን ነገሮች ለመቅረፍ ዕርዳታ ይለግሣል:: የባለሙያዎች ተንቀሳቃሽ ቡድኖች በርካታ የኢትዮጵያዊያን ወጣቶች በሚገኙበት አካባቢዎች ድረስ በመሄድ ዕርዳታና በመልካም የሕይዎት ጎዳና ለመምራት ምክር ለመለገስ ወጣቶች በተከማቹበት ቦታ ተገኝተው ወጣቶችን ያነጋግራሉ:: እነዚህ የባለሙያዎች ተንቀሳቃሽ ቡድኖች የሚሰሩት ከአዳሪ ትምህረት ቤቶችና ከትምህርት ቤቶችና ከወጣቶች ጋር ከሚሠሩ የአካባቢ ሠራተኞች ጋር በመተባበር ነው:: እነርሱም ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎችና ሙያዊ ዕርዳታዎችን ይሠጣሉ:: እነዚህም ሠራተኞች የተለያዩ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው::